የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከወጣው መመሪያ ላይ የተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ

መስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከጤና ሚኒስቴር እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ዓለም ዓቀፍ ወረርሽኝ የሆነውን እና በሃገራችንም የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት ለመግታት እና ለመቆጣጠር የሕብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል አቋቁሞ መጠነ ሰፊ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። ከዚህም ባለፈ በሃገራችን የተለያዩ ክፍሎች የሕብረተሰብ ጤና ስጋቶች ላይ የቁጥጥር እና ምላሽ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

በመሆኑም የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና የሚያስከትለው ጉዳት ለመቀነስ ስለ ሚወሰዱ ክልከላዎች እና ግዴታዎች በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመድኃኒትና ምግብ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 72 ንዑስ-አንቀፅ (2)፣ በምግብ፣መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661 አንቀፅ 55 ንዑስ-አንቀፅ (3) እና የምግብ፣የመደኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሰረት መመሪያ ቁጥር 30/2013 የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ አውጥቷል።ስለሆነም የወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጋዜጣዊ መግለጫ ተዘጋጅቷል።

ማንኛውም ኮቪድ-19 ያለበት ሰው ቫይረሱ እንዳለበት እያወቀ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፣በእጅ መጨባበጥ፣የእርስ በእርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ የተከለከለ ሲሆን፣ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ መገኘት ወይም መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፤ ሆኖም ዕድሜያቸው ከስድስት አመት በታች የሆነ ህጻናት ወይም በማሰረጃ የተረጋገጠ የመተንፈሻ አካላት ወይም መሰል ችግር ያለባቸው ሰዎች ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንባቸውም።

ማንኛውም መንግስታዊ የሆነና መንግስታዊ ያልሆነ የግል ተቋም ሰራተኞች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት መስጠት አይችሉም። እንዲሁም የንግድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ላላደረገ ሰው አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፤ በማንኛውም አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቦታዎች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ የተከለከለ ነው።

ማንኛውም የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት እንዲሁም የግልና የመንግስት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የፊትለፊት ትምህርት መስጠት መጀመር እንደሚቻል ሳይወሰን እንዲሁም ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ወይም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ በመመሪያ የሚወጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሌሎች ዝርዝር የትምህርት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ሳይከተል ትምህርት መስጠት የተከለከለ ነው።እንዲሁም ማንኛውም የህጻናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎት

መስጠት እንደሚቻል ሳይወሰን አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ የሚወጡ ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር አገልግሎት መስጠት አይችልም።

ማንኛውም ኮቪድ 19 በሽታ አለብኝ ብሎ እራሱን የሚጠረጥር ሰው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ የመመርመርና ቫይረሱ ወደ ሌሎች እንዳይተላፍ አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፣በተለይም በሽታው አለበት ተብሎ የሚጠረጠርን ሰው ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

ማንኛውም አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስታዊም እና የግል ተቋም አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ ተቋሙ ለሚመጡ ተገልጋዮች ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ ተገልጋዮች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልክት የማድረግ እና ተገልጋዮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን መተግበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሀገር አቀፍም ሆነ የከተማ ውስጥ ትራንስፖርትን በተመለከተ በህግ ከተወሰነው የመጫን አቅም ልክ ሰዎችን የመጫን፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያላደረጉ ሰዎችን አገልግሎት መስጠት የሌለበት ሲሆን፣ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አሰሪዎች በተመለከተ በግንባታ ሳይቶች ላይ አስፈላጊውን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ እንደ ውሃ፣ ሳሙና፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ሳኒታይዘር ወይንም አልኮል፣ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የጸረ ተህዋሲያን ግብዓት የሚሟላት ግዴታ አለበት።

በሆቴል፣ በአስጎብኚነት እና በሌሎችም የቱሪዝም መስክ የተሰማሩ ተቋማት በሰራተኞቻቸው እና ተገልጋዮቻቸው መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት እንዲኖር የማድረግ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን የመቆጣጠር፣የመከላከያ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀት ግዴታ አለባቸው።

የድንበር ላይ ጤና ቁጥጥርን በተመለከተ፣ድንበር አቋራጭ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች፣ የኢትዮ ጂቡቲ የባቡር ትራንስፖርት አሽከርካሪዎችና ረዳቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች በኩል የኮሮና ቫይረስ የ RT PCR ምርመራ ውጤት ይዘ የሚመጡ መንገደኞን፣.በየብስ ድንበር በኩል የሚገቡ ሰዎችን፣ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ግዴታዎችና ሃላፊነቶች በተመለከተ መመሪያው ሰፊ ማብራሪያ አካቷል።

በቤት ውስጥ ማቆያ እና ክብካቤ ወቅት መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ ፣ በቤት ማቆያ እና ክብካቤ ላይ የሚገኝ የኮቪድ 19 ታማሚ ወይም በኮቪድ-19 በሽታ ተይዟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው የሚከተላቸውን ጥንቃቄዎች፣ኳራንቲን ስለሚደረጉ ሰዎች፣ አስከሬን በተመለከተ፣ስለ ሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ሃይማኖታዊ እና የአደባባይ በዓላት አከባበርን በተመለከተ እንዲሁም የጭፈራ፣ሲኒማ፣ቲያትር እና የስዕል ጋላሪ ቤቶች ተግባራዊ ማድረግ ስለ ሚገባቸው ቅድመ ጥንቃቄዎች የሚመለከቱ ጉዳዮችን በመመሪያው በዝርዝር ቀርበዋል።

በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚገኙባቸው ተቋማት ላይ የተጣሉ ክልከላዎች እና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች በተመለከተ የወረርሽኙ ስርጭት ያለበት ሁኔታ በየጊዜው እየታየ በሌላ መመሪያ እስኪወሰን ድረስ የአረጋዊያን የመጦሪያ ስፍራዎች እና የማገገሚያ ማዕከላት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን በአካል መጠየቅ የተከለከለ ነው።

በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የዘርፉ መስርያ ቤቶች በየመስካቸው የሚያወጧቸው መመርያዎችና አሰራሮች የኮቪድ 19 በሽታን ለመግታት ወይም ለመቀነስ በወጣው መመርያ ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የማይቃረኑና ተጣጥመው የወጡ መሆን አለባቸው፣

በመመሪያ የተደነገጉ ክልከላዎችን እና ግዴታዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል። በመሆኑም ማንኛውም ሰው ከ 25/01/2013 ጀምሮ መመሪያው የጸና መሆኑን አውቆ ተግባራዊ እና ተፈፃሚ እንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ ያሳውቃል።